# ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልና

# አራቱ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ቃለ መሐላ ፈፀሙ።

ትናነትና ጧት በከፍተኛ ድምቀት የተከፈተው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ጉባዔ በዛሬ ውሎ የመረጣቸው ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የፓርቲው ፕሬዚዳንትና አራቱ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ቃለ መሐላ ፈፀሙ።



ቃለ መሐላ የፈፀሙት አራቱ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ የምሥራቅ ቀጣና ኃላፊ፤ አቶ አባይነህ ብርሃኑ የሰሜን ቀጣና ኃላፊ፤ ዶክተር ታዴዎስ ቦጋለ የደቡብ ቀጣና ኃላፊና አቶ አሰፋ ሀብተወልድ የምዕራብ ቀጣና ኃላፊ ናቸው።

በዚህ ቃለ መሐላቸው ፕሬዝደንቶቹ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ እንደሚከፍሉ አረጋግጠዋል።